**ጥር/2013 ዓ.ም**

## የፍልሰት ተጎጂዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

### መግቢያ

በሰው የመነገድ፣ ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና ሰውን ለስራ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የመላክ ወንጀሎች በተደራጀ፣ ውስብስብና ረቂቅ በሆነ መንገድ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ወንጀሎች የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብቶች በመግፈፍ ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ከመዳረግም ባለፈ እስከ ሞት የሚደርስ ጉዳትን ሊያስከትሉ የሚችሉ የወንጀል አይነቶች በመሆናቸው ወንጀሎቹን ለመከላከልና የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ የአገራትን ቁርጠኝነትና ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቁ የወንጀል አይነቶች መሆናቸው የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው፡፡

ከወንጀሎች አስከፊነትና ውስብስብነት በመነሳት ወንጀሉን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አገራት በተናጠል ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ የአገራት መተባበርን ውጤታማ ለማድረግ የተባበሩት መንግስታት ሁለት ፕሮቶኮሎችን አውጥቷል፡፡ ኢትዮጵያም በሰዎች መነገድ በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት እና ሰዎችን  በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህርና በአየር ማስወጣትና ማስገባት ለመከላከል የወጡትን እነዚህን ፕሮቶኮሎች እንደቅደም ተከተላቸው በአዋጅ ቁጥር 737/1999 እና 736/1999 በማጽደቅ የማስፈፀም ስልጣኑን ለቀድሞው የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ላሁኑ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሰጥታለች፡፡
ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ መኖር፣ የተደራጀና ወጥነት ያለው የትብብር፣ የቅንጅት እና የህግ ማስከበር ተግባር፤ እንዲሁም ተጎጅዎችን መልሶ የማቋቋም ስራ በአግባቡ የሚሰራበትን ስርዓት መዘርጋት  አስፈላጊ መሆኑን እሙን ነው፡፡

በዚህም መሰረት አሁን በመተግበር ላይ የሚገኘው በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ቀድመው ከነበሩት ህጎች በተሻለ ሁኔታ ወንጀሎቹን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለተጎጅዎች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግና መልሶ ለማቋቋም በሚያስችል መልኩ

የተዘጋጀ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ብሄራዊ ምክር ቤቱ ተጎጂዎችን ማዳን፣ መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከተ አገር አቀፍ የቅብብሎሽ ስርዓት መመሪያ እንደሚያወጣ በአዋጁ አንቀጽ 34(2) ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት የአዋጁን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ይህ የፍልሰት ተጎጂዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

1. <u>የተከናወኑ የማርቀቅና ድህረ ማረቀቅ  ተግባራት</u>

ረቂቁ በጉዳዩ ላይ በቅርበት ከሚሰሩ ተቋማትና ከፍልሰት የትብብር ጥምረት ጽ/ቤት በተውጣጡ ባለሙያዎች የተዘጋጀ ሲሆን ረቂቁ ከተጠናቀቀ በኋላም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ያሳተፉ የውይይትመድረኮችን በማመቻቸት ግብዓት እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ የተገኘውን ግብዓት በማካተት ረቂቅ መመሪያው እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

2. <u>የረቂቅ መመሪያው አስፈላጊነት</u>

በሰው የመነገድና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 መሰረት የተቋቋሙት ብሄራዊ ምክር ቤት እና የትብበር ጥምረት ውስጥ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የሀይማኖት ተቋማት በአባልነት ይሳተፋሉ፡፡ እነዚህ አካላት ተጎጂዎችን በማዳን፣ መልሶ በማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ በመስጠትና ከህብረተሰቡ ጋር በመቀላቀል በተለያየ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን የእነዚህ አካላትን ኃላፊነትና የቅብብሎሽ ሂደት በሚያሳይ መልኩ መመሪያ ማዘጋጅት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3. <u>የረቂቅ መመሪያው ቅርጽና ይዘት</u>

   3.1 <u>የረቂቅ መመሪያው ቅርጽ</u>

መመሪያው በአጠቃላይ 4(አራት) ክፍሎችን እና 13 (አስራ ሶስት) አንቀፆች እንዲኖሩት ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ክፍል አንድ የመመሪያውን ጠቅላላ ድንጋጌ (አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ ፣ አንቀጽ 2 የቃላትና ሃረጋት ትርጓሜን፣ አንቀጽ 3 የተፈጻሚነት ወሰንን፣ አንቀጽ 4 ዓላማን እና አንቀጽ 5 ደግሞ ጠቅላላ መርሆዎችን) ይይዛል፡፡

የረቂቅ መመሪያው ክፍል ሁለት በአጠቃላይ ስለ ብሄራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓቱ የያዘ ሲሆን በውስጡም የቅብብሎሽ ሥርዓቱ ስለሚይዛቸው ጉዳዮች (አንቀጽ 6) ፣ በቅብብሎሽ ስርዓቱ የተቋማት የወል የተናጠል ተግባርና ሀላፊነቶችን በዝርዝር (አንቀጽ 7 እና 8) ደንግጓል፡፡

ክፍል ሶስት ደግሞ ስለ ክትትልና ድጋፍ የያዘ የረቂቅ መመሪያው የመጨረሻ ክፍል (ክፍል አራት) ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የሚሸፍን ሲሆን ከአንቀጽ 10 እስከ አንቀጽ 13 ያሉትን የመጨረሻ ድንጋጌዎች ይይዛል፡፡

### 3.2 የረቂቅ መመሪያው ዝርዝር ይዘት

ከላይ በረቂቅ ህጉ ቅርጽ እንደተመለከትነው ረቂቅ አዋጁ በውስጡ 13 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትን አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

I. መግቢያ

ተጎጂዎችን ስለማዳን፣ ስለመመለስ፣ መልሶ ስለማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበትና ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት ሁኔታ ያለው አሰራር ግልጽነት የሚጎድለው፣ ሰፊ ክፍተት ያለበት እና ቅንጅታዊ አሰራርን ያልተከተለ መሆኑን እና በእነዚህ የቅብብሎሽ ሂደቶች ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን እና የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ መለየት እና ዝርዝር አሰራራቸውን መወሰን፤ እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖረውን የተጎጅዎች የቅብብሎሽ ሥርዓት እና የቅብብሎሽ ሥርዓቱ የሚሸፍናቸውን ጉዳዮች በዝርዝር መወሰን ያለውን ሚና በሚያሳይ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም የመመሪያውን ዝርዝር ድንጋጌዎች ከመመሪያው ዓላማ አንጻር ለመቃኘትና ለመረዳት ያግዛል፡፡

II. አጭር ርዕስ

የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 1 የመመሪያውን አጭር ርዕስ (መጠሪያ ስያሜ) የያዘ ሲሆን በአዋጁ መሰረት የወንጀል ተጎጂዎች ጉዳት የሚደርስባቸው ከፍልሰት ጋር በተያያዘ በመሆኑና በአጠቃላይ ብሄራዊ ምክር ቤቱ እና የትብብር ጥምረቱ በአዋጁ ከተሰጣቸው ኃላፊነት ሥፋት አንጻር “የፍልሰት ተጎጂዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር---/2012” የሚል ሥያሜ እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

III. ትርጓሜ

የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 2 በመመሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጋት በመመሪያው አተገባበር ላይ የሚኖራቸውን ትርጉም ያስቀመጠ ነው፡፡ ይህ አንቀጽ 6

ንዑስ አንቀሶችን የያዘ ሲሆን በአንቀጽ 2(1) አዋጅ ማለት አዋጅ ቁጥር 1178/2012 እንሆነ፣ ተጎጂ ወይም የፍልሰት ተጎጂ ማለት በአዋጁ ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የተፈጸመበት እና አካላዊ፣ ስነልቦናዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ወይም እነዚህ ጉዳቶች የደረሱበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ባይሆንም ለወንጀሉ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተመለከተው ጥበቃ እና ድጋፍ እንደ አግባብነቱ የሚያስፈልገው ሰው ማለት እንደሆነ (አንቀጽ 2/2)፤ ፍልሰት ማለት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የሰው ወይም የሰዎች እንቅስቃሴ ማለት እንደሆነና ስደተኞችን፣የተፈናቀሉ ሰዎችን፣ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞችን እና ሌሎችን እንዲሚያጠቃልል ተደርጎ ተተርጉሟል (አንቀጽ 2/3)፡፡ አንቀጽ 2(4) ደግሞ ፖሊስን የክልል ወይም የፌዴራል ፖሊስ ነው በማለት ተርጉሞ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በፍልሰት ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደየአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ተደንግጓል፡፡ በመጨረሻ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ እንደሚያካትት ትርጓሜ ክፍል ውስጥ ተደንግጓል፡፡

## IV. የተፈጻሚነት ወሰን

የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 3 የመመሪያውን የተፈጻሚነት ወሰን የሚደነገግ ሲሆን በአዋጁ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ወይም በሌላ አግባብ ተጎጂዎችን የማዳን፣ የመመለስ፣ መልሶ የማቋቋም፣ ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀል እና ልዩ ልዩ ድጋፍ የማድረግ ተግባር እና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት፤ እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት በሚያከናውኗቸው ተጎጂዎችን የማዳን፣ የመመለስ፣መልሶ የማቋቋም እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖር ተደርጓል፡፡

## V. የመመሪያው ዓላማ

አንቀጽ 4 የመመሪያውን ዓላማ ያስቀምጠ ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መመሪያው የፍልሰት ተጎጅዎችን ማዳን፣ መመለስ፣ መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት ሁኔታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የተቋማትን ሚና በመለየት እና ውጤታማ የቅብብሎሽ ሥርዓት በመዘርጋት፤ ወጥ፣

ተገማች፣ ተደራሽ እና ፍትሐዊ የሆነ የፍልሰት ተጎጅዎች ድጋፍና ጥበቃ እንዲኖር ማስቻል እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

## VI. ጠቅላላ መርሆዎች

የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 5 የቅብብሎሽ ስርዓቱ የሚመራባቸውን ጠቅላላ መርሆዎች የደነገገ ሲሆን የተጎጂዎች ሙሉ ፈቃድ፣ እኩልነት/ያለማዳላት፣ የተጎጂዎችን የግል ፍላጎት ያማከለ መሆን፣ የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞችን ለአደጋ ተጋላጭነትና ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን፣ ግላዊ ሚስጢራቸው እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ መሆን፣ ፍትህዊነት፣ አሳታፊነት፣ ተጠያቂነት እና ቅልጥፍናና ውጤታማነትን በመርህነት አስቀምጧል፡፡

## VII. የቅብብሎሽ ሥርዓቱ ስለሚይዛቸውን ጉዳዮች

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 6 ሥር የቅብብሎሽ ሥርዓቱ የሚይዛቸውን ጉዳዮች የሚሸፍን ሲሆን በዚህም መሰረት ተጎጂዎችን ማዳን፣ተጎጂዎችን መመለስ፣ ተጎጂዎችን ከህብረተሰቡ ጋር ማቀላቀል እና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም ይገኙበታል፡፡

## VIII. የተቋማትን የወልና የተናጠል ተግባርና ሀላፊነቶች

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 7 እና 8 በቅብብሎሽ ስርዓቱ ውስጥ የተቋማትን የወልና የተናጠል ተግባርና ሀላፊነቶችን በዝርዝር የሚያሳዩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ተቋማትን በቅብብሎሽ ሂደቱ ውስጥ በህግም ሆነ በሌላ አግባብ የተሰጣቸውንና የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ሃላፊነት መነሻ በማድረግ የተመረጡ ሲሆን የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒሰቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ፖሊስ ፣ የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ ጤና ሚኒስቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ የፌዴራል ከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ የገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሰሩ በየደረጃው ያሉ ተቋማት፣ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፣ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች በዝርዝሩ እንዲካተቱ ተደርጎ ተደንግጓል፡፡

የእነዚህ ተቋማትን የወል ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ በአንቀጽ 7 ስር በቅብብሎሽ ሂደቱ ዉስጥ አንድ ተቋም መስጠት ያለበትን አገልግሎት ለተጎጂው ሰጥቶ በተቋሙ የማይሸፈኑ አገልገሎቶችን በተመለከተ የተጎጂውን መረጃ፣ የሰራውን ሥራ እንዲሁም የተገኙ ውጤቶችን በመመዝገብ አገልግሎቱን ከሚሰጥ አግባብነት ካለው አገልግሎት ሰጪ ተቋም ጋር ማገናኘት እንደሚኖርበት፤ መረጃ የመለዋወጥና ተባብሮ የመስራት ሃላፊነት እንዳለባቸው፤ የቅብብሎሽ ስርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የዓሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት እንደሚችሉ፤ በተጎጂዎች ላይ ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ ነገሮች ካሉ ለሚመለከተው የፍትህ አካል ማሳወቅ እነዳለባቸው የሚደነግጉ ንዑስ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡

አንቀጽ 8 ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩ ተቋማትን የተናጠል ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር የያስቀመጡ 12 ንዑስ አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡ በመዚህም መሰረት ንዑስ አንቀጽ 1 የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጪ ሀገር የሚገኙ የተጎጂ ኢትዮጵያውያንን መረጃ፣ የሚገኙበትን አገር፣ ያሉበትን ሁኔታ (ታስሮ ወይም ተይዞ የሚገኝ ከሆነም ባለበት አገር የሚገኝ ወይም በቅርበት የሚሰራ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂው እንዲለቀቅ ጥረት የማድረግ) እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ እንዳለበት፤ ተጎጂው ውጭ ሀገር እንዳለበት እና የጉዞ ሰነድ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ተጎጂዎች በራሳቸው ፈቃድ ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ በማድረግ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደሚያስረክብ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ተጎጂዎችን የመመለስ ሂደትም የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ ተጎጂዎች የይለፍ ሰነድ እንዲያገኙ የማድረግ ሃላፊነት ያለበት (አንቀጽ 8(2)) ሲሆን ኤጀንሲው በተጨማሪም ከኢትዮጵያ መውጫና ወደ ኢትዮጵያ መግቢያ ተብለው በተለዩ የድንበር ኬላዎች ላይ ተጎጂዎችን የመለየትና የመመዝገብ ስራዎችን እንደሚያከናውንና መረጃውንም ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒሰቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶችም በሀገር ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎችን፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ የማጠናቀርና ፣ ለሚመለከታቸው አካላት የማድረስ፣ በሀገር ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ከወጪ አገር የተመለሱ ተጎጂዎችን የድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ ፍላጎት በመለየት አግባብነት

ካላቸው መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግ፤ የተጎጂዎችን ጠቅላላ የፍላጎት ጥናት በማድረግ ማህበራዊና የስነ ልቦና ምክር አገልግሎት የመስጠት፤ በተቋሙ የማይሸፈኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ አገልግሎቶቹን ወደሚሰጡ ተቋማት የመላክ እና በሀገር ውስጥ ወደ አካባቢያቸው መመለስ የሚፈልጉ ተጎጂዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ወደአካባቢያቸው እንዲመለሱ የማድረግ ስራዎችን እንደሚሰራ በመመሪያው ተደንግጓል (አንቀጽ 8(3))፡፡ ፖሊስ ድንበር ሊያቋርጡ ሲሉ የተገኙ ተጎጂዎችን ለድጋፍ ሰጪ ተቋማት የመላክና ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ መረጃዎች ካሉ ምርመራ የማድረግ፤ በወንጀል በምርመራ እና በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት የተጎጂዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ የማድረግ፤ ተጎጂዎች ሰብዓዊ በሆነ መንገድ የመያዝ መብታቸውን እንዲሁም ስለ ምርመራ ሂደቱ መረጃ የማግኘት መብታቸውን የማረጋገጥ፤ በወንጀል በምርመራ እና በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ተጎጂዎች በማናቸውም ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት እንዳይቆዩ ክትትል ያደርጋል፣ ይህ ሆኖ ሲገኝየማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ የማድረግ ፤ ምስክር ወይም ጠቋሚ በመሆኑ ምክንያት የተጎጂው ወይም የቤተሰቡ ህይወት ወይም ንብረት ለአደጋ የተጋለጠ እንደሆነ በምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 መሰረት ተገቢ ጥበቃ የሚያገኝበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ ተጎጂዎች ቃል-መጠይቅ ከማድረጋቸው በፊት ቃለ መጠይቁን ለመስጠት ፈቃደኛና ብቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤ እና የተጎጂውን ሁኔታና ፍላጎት ከግምት በማስገባት የተሻለ ድጋፍ እና እንክብካቤ ወደሚያገኝበት ተቋማት መላክን አካቶ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶችም ተጎጂ ህጻናትን በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ዝርዝር ተግባራት ተሰጥቷቸዋል፡፡ለምሳሌም፡ ህጻናትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር የማገናኘትና በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጡ ድጋፎች የሴቶችና ህጻናትን ልዩ ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ መሆናቸውን የመከታተል ኃላፊነት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ የጤና ሚኒስቴርና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶችም ከጤና አንጻር በህግና በተግባር ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች አንጻር ለተጎጂዎች መስጠት ስለሚገባቸው አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

የጠቅላይ ዐቃቤ ህግና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ተጎጂዎች ከምርመራ በፊት፣ በምርመራ ወቅት፣ በፍርድ ሂደትና ከፍርድ በኋላ ስላሏቸው ዝርዝር መብቶች እና ግዴታዎች  የምክር አገልግሎት ከመስጠት ጀምሮ የተጎጂዎችን መብት ከመጠበቅና ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር ዝርዝር ተግባራት ተሰጥተውታል፡፡

ተጎጂዎችን በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ከማስቻል አንጻር እንደየስራ ድርሻቸው የፌዴራል ከተሞች ሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፤ የገጠር የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሰሩ በየደረጃው ያሉ ተቋማት፤ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ እና የክልል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች፤ እንዲሁም አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች ሊሰሩ የሚገባቸውን ተግባራትና ኃላፊነቶች በዝርዝር እንዲደነገጉ ተደርጓል፡፡

## IX. የድጋፍ ክትትል ስርዓት

በዚህ ክፍል ለብሄራዊ ምክር ቤቱ ተጠሪ የሆነው የትብብር ጥምረት ይህ መመሪያ በትክክል ስራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ፤ ለዚህም የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ፣ ሪፖርት የመሰብሰብና አፈጻጸሞችን የማስገምገም በመመሪያው አፈጻጸም የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችን የመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫ የማስቀመጥእና በመጨረሻም ለብሄራዊ ምክር ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ ተግባርና ኃላፊነቶች እንዳሉት ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የክልል የፍልሰት ትብብር ጥምረቶች ይሄንን መመሪያ መሰረት በማድረግ እንደየክልላቸው ነባራዊ ሁኔታ የቅብብሎሽ ስርዓት መመሪያ ሊያወጡ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡

## X. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

በመጨረሻም የረቂቅ መመሪያው ክፍል ሦስት ልዩ ድንጋጌዎች እንዲይዝ ተደረጎ የተቀረጸ ሲሆን በውስጡም ማንኛውም አካል መመሪያውን ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ እንዳለበት፣ በመመሪያው ሀላፊነት የተሰጣቸው አካላት ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆኑ፤ መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ እና መመሪያ ተፈጻሚ መሆን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይሸፍናል፡፡